


AMHARIC

مؤسسة دبي
لرعاية النساء والأطفال
DUBAI FOUNDATION FOR WOMEN & CHILDREN

## ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ምን ማለት ነው

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ሰዎችን (ተጠቂዎችን)በግድ ወይም በማስፈራራት ጠልፎ፣ አጭበርብሮ፣ አታሎ ወይም በሌላ መንገዶች መመልመል፣ ማዘዋወር፣ ማቆየት፣ሲሆን ይህም በግዳጅ ለወሲብ፣ ለግዳጅ ሥራ፣ለባርነት ፣ እንዲሁም የአካል ክፍሎች ለመውሰድ ሲባል ሰዎችን ማዘዋወር ማለት ነው።

### ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎች መስፋፋት፣

የሰዎች ዝውውር ወንጀል በአለምአቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ ይገኛል። እነዚህ አገሮች የዝውውር ምንጭ፣ መተላለፊያ፣ ወይም መድረሻ አገሮች ይባላሉ። ተጠቂዎች በመጀመርያ የሚመጡባቸው አገሮች ወይም መነሻ ምንጭ አገሮች ይባላሉ። መድረሻ አግሮች ደግሞ ተጠቂዎች በመጨረሻ ለስራ፣ ለጉብኝት፣ ወይም ለትምህርት መሄድ የሚፈልጉበት አገሮች ናቸው። በአብዛኛው በተጠቂዎች ላይ አደጋ የሚደርሰው መተላለፍያ አገሮች ላይ ሲሆን መተላለፍያዎች ተጠቂዎች የሚተላለፉበት አገሮች ናቸው፡ ፡ ይኸውም የሰዎች አዘዋዋሪዎቹ ተጠቂዎች ወደ የሚሄዱበት አገር ከመድረሳቸው በፊት ለመዘዋወር ይሞክራሉ።

## ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የበለጠ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች፧

**የህገወጥ ሰዎች አዘዋዋሪዎች በአብዛኛው የሚያጠቁት፧**

- ሴቶች እና ልጆች
- ማንበብ እና መጻፍ የማይችሉ ሰዎች
- በቂ ትምህርት እውቀትና አስተውሎት የሌላቸው ሰዎችን
- ስለ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ያልሰሙ ወይም የማያውቁ ሰዎች
- በችግር ላይ ሆነው ራሳቸውን ለማሻሻል እየሞከሩ ያሉ ሰዎች
- መብታቸውን የማያውቁ፣ በተለይ በስራ ፍለጋ እና ስምምነት ወቅቶች
- የሥራ እድል ፍለጋ ከአገር ለመውጣት ሲያስቡ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ የሚሉትን በጭፍን የሚያምኑ ሰዎች
- የራሳቸውን ወይም የቤተሰቦቻቸዎን ንብረት ሸጠው ወደ ውጭ አገር መጓዝ የሚፈልጉ ሰዎች።

**መከላከል**

## ከሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዴት እራስን መጠበቅ ይችላሉ?

- በግንኙነት ወቅት ኢንተርኔት ብቻ የሚጠቀሙ ኩባኒያዎችና ወኪሎቻቸው በተንቀሳቃሽ ስልክ ብቻ ግንኙነት የሚያደርጉ ኩባንያዎችን መጠንቀቅ።
- የስራ ችሎታቸሁን ሳይመዝኑ፤ ወረቀት፣ ቪዛ፣ ወይም የጉዞ ቲኬት እና መኖርያ እንሰጣችሁዋለን የሚሉ የስራ ቀጣሪዎችን መጠንቀቅ። ይህን የመሰለ አጓጊ ስራዎች ማጭበርበር እና ለሕገ፡ወጥ የሰው ዝውውር ሊሆን ይችላል።
- ለስራ መጓዝ ስታስቡ፣የመግቢያ ቪዛ ምን መምሰል እንዳለበት አረጋግጣቸሁ የተሰጣችሁን ፍቃድ ትክክልነት ማየት።
- ከሐገር ሲወጡ የተጭበረበሩ ሰነዶችን በምንም አይነት ጉዞ ላይ አለመጠቀም።
- የሐሰት ስራ እና ሰራተኛ አገናኝ መጠንቀቅ። የአገናኝ ኩባንያ ህጋዊነት ለመጓዝ ባሰባችሁበት አገር ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጋር በመሔድ በማረጋገጥ።
- የስራ ውሎችን በደንብ ማንበብ መፈተሽ (ምሳሌ፡ ሥራ ዓይነት፣ ክፍያ፣ የስራ ሰአት፣ እረፍት፣ የስራ ስምምነት ሲያበቃ የሚያገኙት ጥቅማጥቅም መኖርያ፣ ሕክምና እና ኢንሹራንስ ስምምነቱ ውስጥ በትክክል መከተቱን ማረጋገጥ)።

- በማያውቁት ቋንቋ የተፃፈ ኮንትራት አለመፈረም። ቀጣሪው ድርጅት በሚያውቁት ቋንቋ ኮንትራት እንዲያዘጋጅ እና በየኮንትራክቱ አላስፈላጊ አንቀጾች ላይ ማብራርያ እንዲያደርጉ መጠየቅ፣ እነዚህም፦

  1. ስራ መጀመሪያ ቀን
  2. የስራው አይነት እና ሁኔታ
  3. የስራው ቦታ
  4. የስራው አተገባበሩና መመሪያ
  5. ክፍያ

  (በUAE ውስጥ የኮንትራክቱን አረብኛ ቅጂ መያዝ ይኖርባቸዋል ይህውም በኮንትራክቱ ወቅት አለመግባባት ቢፈጠር ፍርድ ቤት መቅረብ ሊኖር ስለ ሚችል)።

- የሰው እሴት እና ሥነምግባርን ለመጠበቅ ሁል ጊዜ ንቁ ይሁኑ። ህገ ወጥ ወይም ሥነ ምግባር የጎደለው ስራ እንዲሰሩ ከተጠየቁ፣ ስራውን ወድያው አቁማችሁ ባለባችሁት አገር ለሚመለከተው ባለሥልጣን ወይም ቡድን ያሳውቁ።

- ፓስፖርታችሁ እና የመታወቅያ ወረቀቶች በተለይ ማንም ሊደርስበት በማይቻልበት ቦታ ያድርጉ፤ ይህን በማድረግ ተገቢ ያልሆነ ጫናዎች መቋቋም ይችላሉ። እንዲሁም በኮፒም ቅጂ አድርጋችሁ ሌላ ሰው መድረስ በማይችልበት ቦታ ማስቀመጥ።

- የመኖርያ አድራሻ እና አካባቢያችሁን በደንብ ማወቅ ይጠበቅባችዋል። አስፈላጊ ስልክ ቁጥሮችን እንዳይረሱ (ለምሳሌ ፖሊስ፣የ ሐገር ኤምባሲ፣ አምቡላንስ፣ የሰብአዊ መብት ድርጅት፣ የዜግነት መምሪያ፣ የሠራተኛ ሚኒስቴር እና ሌላ ተገቢ ባለሥልጣናት የስልክ ቁጥሮች ይያዙ)
- ሰብአዊ መብቶችን በመጠበቅ እና በሕግ በማካተት UAE ከታወቁት አገሮች አንዱ ነው። አግባብነት የሌለው ስራ ወይም ማስፈራራትን አትቀበሉ። በማንኛውም ወቅት ሊረዷችሁ የሚችሉ የሕግ አካላት (ምሳሌ፥ ፖሊስ፣ ኤምባሲ፣ እና የአገራችሁ ቆንስላ ተወካይ) መኖራቸውን ማወቅ አለባችሁ።
- የግል ስልክን ለሌላ ሰው አሳልፈው ባለመስጠት በተገቢ መንገድ ይጠቀሙ። ከስልካችሁም በተጨማሪ አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮችን ለምሣሌ ሊረዳዎት የሚችል ሰው ዘመድ የቅርብ ጓደኛ ቁጥሮችን በተለይ ማስታወሻ ደብተር ላይ በጽሑፍ ይያዙ። አነዛን ቁጥሮች በችግር ጊዜ መጠቀም ትችላላችሁ።
- እንደገና አስታውሱ፣ ቤተሰቦቻችሁ ያላችሁበትን አድራሻ እና የምትሰሩበትን ቦታ እና ስራ ካወቁ፣ እናንተን ለማግኘት እና ለመርዳት ይቀላቸዋል። ይህን በማድረጋችሁ የሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂ እንዳትሆኑ ይረዳችኋል።

## የሕገ-ወጥ ሰው ዝውውር ተጠቂ ከሆናችሁ፥

- በተቻላችሁ ሁሉ ራስን ማውረድ እና ብዝበዛ ታገሉ። እሴታችሁን፣ ሃይማኖታችሁን፣ እምነታችሁን፣ ደንባችሁን የሚቃረን ተግባርን አትፈጽሙ።
- በደላላዎች በሚደረገው ጫና እና ማስፈራራት አትንበረከኩ፣ የሚናገሩት እውነት አይደለምና።
- ችግር ቢደርስባችሁ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ እና ከምትቀርብዋቸው ሰዎች እርዳታ ጠይቁ።
- ለጓደኞች ወይም ቤተሰብ የደረሰባችሁን ችግር መንገር፣ እነሱም ለሚመለከተው አካል ችግራችሁን በመግለፅ ሊረዷችሁ ይችላሉ።

## ለድንገት አስፈላጊ ስልክ ቁጥሮች፥

| ድርጅት | ቁጥር |
| --- | --- |
| ዱባይ ሴቶች እና ልጆች ድርጅት | 800-111 |
| የEwa’a ስልክ | 800-7283 |
| ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ክፍል - ዱባይ | 8005005 |
| ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ፀረ ክፍል - ዱባይ ፖሊስ | 04-2036215 |
| የሠራተኛ ሚኒስቴር | 800-665 |

مؤسسة دبي
لرعاية النساء والاطفال
DUBAI FOUNDATION FOR WOMEN & CHILDREN

Tel: +971 4 6060300
www.dfwac.ae
Fax: +971 4 2871177
P.O.Box: 97727 Dubai, UAE